*Ethiopian Sport & Culture Federation in Europe*

**በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን፤**

## ከአውሮፓ የስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን የተሰጠ መግለጫ

በመጀመሪያ በአውሮፓ የአትዮጵያውያን ስፖርትና የባህል ፌዴሬሽን የከበረ ሰላምታውን ለእናንተ ለወገኖቹ እያቀረበ በመቀጠልም ይህ የአውሮፓ ስፖርትና የባህል ፌዴሬሽን የመጀመሪያ እና ዋነኛ አላማ በመላው አውሮፓ ተበታትኖ የሚኖር ወገን ተሰባስቦ ወገናዊ ስሜቱን የሚገልፅበት፣ የኑሮ ልምድ ልውውጥና የህይወት ገጠምሽኖች የሚቀያየርበት ከዛም ባሻገር በየጊዜው ቁጥሩ እጅግ እየጨመረ የሚመጣውን አዲሱ ተተኪ ትውልድን ስለ ሀገሩ፣ ስለ ወገኑ፣ ስለ ድንቅ ባህላችን የምናስተዋወቅበት መድረክ ለመፍጠር ነው።

ወገኖች! እኛ ሰዎችን ከሌላው የእግዛብሔር ፍጥረታት ለየት የሚያደርገን ማሰብ፣ ማስተዋል፣ ጥሩውንና መጥፎውን መለየት መቻላችን ነው። ዛሬ በአላማችን ላይ የምናያቸው ድንቅና አስገራሚ የፈጠራ ስራዎችን፣ የረቀቁና እጅግ ጥበብን የተላበሱ የስራ ውጤቶች የተሰሩት በእንደኛው አይነቱ ስጋ ለባሽ ሰዎች ነው። ይህም ሲባል ደግሞ የተሰሩት ስራዎች ሁሉ ያለ ድካም፣ ያለ ጥረትና ያለ ምንም ትልቅ ዋጋ ክፍያ የመጡ አልነበሩም። ነገር ግን ድካሙ ድካም የማይመስላቸው ራሳቸውን ለጥሩ ስራ ውጤቶች አሳልፈው በሰጡና መልካም አስተሳሰብ በተላበሱ፣ ከራሳቸው አልፈው ስለ ቀጣዩ ትውልድ በእጅጉ በሚያስቡና ሃላፊነቱም እንደ እራሳቸው አርገው በወሰዱ፣ ፍሬያቸውን ነገ ሊያዩት የማይችሉ መሆኑን እያወቁ እንካን ለመጭው ትውልድ ቅርስ ትተው ማለፍን በሚፈልጉና ቅን አስተሳሰብ ባላቸው ድንቅ የሰው ልጆች የተሰሩ መልካም ስራዎች ናቸው።

ወገኖች! እናማ እኛስ?

- ስንቶቻችን ነን አሁን በተያያዝነው ገድልና ተልዕኮ ለመጭው፣ ለተተኪው ትውልድ ቅርስ ትተን ለማለፍ የምንፈልግ?
- ስንቶቻችን ነን እኔ ዛሬ ተጎድቸ የነገዎቹ ልጆች፣ ልጆቻችን ተደስተው አይቸ የምንል?
- ስንቶቻችንስ ነን እኔ ዛሬ አግኝቸ ሆዴ ጠግቦ አይቸና ታይቸ የምንል? እኔ ከሞትኩ ወዲያ ሰርዶ አይብቀል የምንል?

ሁሉም እራሱን በጥብቅ፣ በጥልቅ ይጠይቅና ፍርዱን ከራስ ማውረድ ይበጃል።
ወገኖች! ዛሬ ያልተቦካ አብሲት ለነገው አፍለኛ እንጀራ ምክንያት እንደሚሆን ሁሉ እኛም ዛሬ ያልተከልነው መሰረት ለነገውና ለተተኪው ትውልድ መዋዠቅና ውድቀት ብሎም ድቀት ይሆናልና ከተጠያቂነት ለመውጣት ራስን ማዘጋጀት ይበጃል። ይህም ሊሆን የሚችለው፤

- ለተሻለና ብዙሃኑን ለሚጠቅሙና ሊያካትቱ የሚችሉ የስራ ውጤቶች አመቸ ሁኔታዎችን መዘርጋት ሲቻል ነው፤
- አሁን ካለንበት የአስተሳሰብ አድማስ ወጣ ብለንና ሰፋ አድርገን ማሰብ ስንችልና ዛሬን ተጎድቶ ለነገ ጠንካራ፣ አስተዋይና ሌሎችን አስታዋሽ ዜጋን ተክቶ ማለፍን መርሆ አድርገን መስራት ስንችል ነው፤

- አብሮ በአንድ ሰሐን መብላትን ብቻ ሳይሆን አብሮ መስራትን፣ መማማርና ተቻችሎ መኖርን ለመቀበል ዝግጁ መሆን ስንችል ነው።

ስለዚህ ሁሉ የመልካም ስራ ውጤቶች ለመዘጋጀት ሆደ ሰፊነት፣ አርቆ አሳቢነት እና ቅንነት የመጀመሪያና ዋነኛ መሰረታዊ ነጥቦች ይሆናሉ። አንድ ስራ፣ የአሰራር መዋቅር ወይንም የአሰራር ሂደት ምንም እንካን ለሁሉም የቀመ ቢሆንም ነገር ግን ሲተገበር ሁሉንም ሊያስደስት እንደማይችል የሚታወቅ ነው።
ይህም ከመሆኑ የተነሳ ሊያነጋግር፣ ሊያስቆጣም ይችል ይሆናል። ነገር ግን አካሄዱ ማዕከላዊነትን፣ ብዙሃኑን በሚያካትት መልኩ የታሰበ ከሆነ ሆድን ሰፋ አድርጎ ለመቀበል መዘጋጀት ይበጃል። አለበለዚያ ግን ለእኔ ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እንደተባለው የዛሬን ብቻ ማየቱ የነገውንም ፍሬ ማቀጨጭ ይሆናልና በዛሬ ስራችን ነገና ከነገም ባሻ ገር ጠንካራ መሰረት ለመጣል ታስቦ ስለሚሆን በትዕግስትና በመቻቻል ውስጥ እንድንመላለስ ይሆን ዘንድ የፌድሬሽናችን መልካም ምናትና ፍላጎት ነው።

ዛሬ ፌድሬሽናችን አድጓል፣ የተሳታፊው ቁጥር ጨምሯል፣ የህዝብ ቁጥር ጨምሯል፣ የህዝብ ፍላጎትና ጥያቄም ጨምሯል አሁን ያለንበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ዋጋ ተከፍሏል። በጊዜው የተከፈለው ዋጋ ፌድሬሽኑን በሁለት እግሩ እንዲቆም ጥርጊያ መንገድን ፈጥሯል። ነገር ግን ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንገመግምና ስንመለከተው የፌድሬሽኑ ዝግጅቶች በተደረጉበት ቦታዎች ሁሉ መጥፎ ትዝታዎችንም ጥሎ አልፎዋል። የፌድሬሽኑ አላማ የሚቃረኑ፣ የጥቂቶችን ፍላጎት ያማሉና በተደረጉት ዝግጅቶችም ትልቅ አለመግባባትን የፈጠረና ህብረተሰቡ ውይንም አዘጋጁ ሳይሆን ግለሰቦች ተጠቃሚዎች ሆነው ማለፋቸው የሚታወቅ ነው። ይህም አይነቱ አካሄድ በአንድ ጊዜ ያላቀመና ከአመት ወደ አመት ችግሮች እየጨመሩ የመጡ፣ ራስ ወዳድ ግለሰቦችም ሁኔታዎችን ለመጠቀም ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ራሳቸውን እያዘጋጁ የመጡ እንደሆነ ውድድሮች የተዘጋጁባቸው ሀገሮች መረጃዎች ይናገራሉ።

- የፌድሬሽኑ አላማ በአውሮፓ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብን ማቀራረብ፣ ማሰባሰብና በትስስር ቤተሰባዊ አስተሳሰብ በውስጣችን እንዲሰረፅ ነው።

- የነገዎቹ የኢትዮጵያ ልጆች በስፖርታዊ ጨዋነት ታንፀው የሚያድጉበትን መድረክ ለመፍጠር ነው። በስፖርታዊ ዲስፕሊን ራሱን የሚያዘጋጅበትና በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮችም ላይ ወገኑን የሚያስጠራበት መንገዶችን ለማመቻቸት።

በጋራ ለነገዎቹ፣ ለተተኪው ትውልድ ስለ ሀገሩ፣ስለ ባህሉ ማስተዋወቅ፣ ሃላፊነትን ማስተማርና ወገኑን አኩሪ፣ ለሀገሩ ተቆርቋሪ ብሎም ተከራካሪ የሆነን ዜጋን ለማዘጋጀት ታስቦ እንጂ አንዱ ፍርደ ገምድል ሌላኛው ተበዳይ እንዲሆን አይደለም። ዛሬ ሳይሆን እራስ ወዳድነት በውስጣችን መስፋፋትን ከጀመረ ሰንበት ብሎዋል። ለዚህም ምስክር ሊሆነን የሚችለው ያሳለፍናቸው የ8 አመታቱ ውድድሮች ይሆናሉ። ምንም እንካን የህዝብ ብዛት እየጨመረ የመጣ ቢሆንም በአንፃሩ ብዙ ሽኩቻዎች፣ አለመግባባትና መለያየትን ፈጥሮ አልፎዋል። ይህም አይነቱ አካሄድ ጤናማ አካሄድ ያልሆነና መቆም ያለበት ለመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተከሰሱትና እየተከሰቱ ያሉት ሁኔታዎች በግልፅ ያሳያሉ። ጥቂቶች ያካበቱበት አብዛኞች ልፋታቸው ባዶ የሆኑበትና እሮሮዋቸውን ያሰሙበት ሁኔታዎች ተከስተዋል። ፍርድ ጎደለ ተመልካች ወገን ተበደለ የሚሉ እሮሮዎችን በየጊዜው መስማት ልማድ ተደርጎዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ቢለፈፍም ሊነገር ቢሞከርም እስካሁን ድረስ ግን እልባት ሊገኝለት አልተቻለም። ምክንያቱም ዛሬ አንዱ አንዱን ቢወቅስ ነገ ደግሞ ተወቃሽ ልሆን እችል ይሆናል ብሎ ከመፍራት የተነሳ መሆኑ ግልፅ ነው።

## ከዚህም የተነሳ የተከሰቱ ችግሮች፤

- ከብዙሃኑ ይልቅ የጥቂቶች መጠቀሚያ ሆኖ ታይቷል፤
- በቡድኖች ላይ ከመጋጨት ሌላ የታየ መሰረታዊ ለውጥ የለም፤
- በቡድኖችም ሆነ በህብረተሰቡም ላይ አለመግባባትን ፈጥሮ አልፏል፤
- ስፖርተኛውም ሆነ ተመልካች ተበዳይ የሆነበትና ቅሬታውን ያሰማበት ሆኖ ታይቷል፤
- አንደኛው ከአንደኛው በጥቂቱ የተሻ ለ ቢመስልም ሃላፊነቱን በሚገባ የተወጣና የገባውን ቃል የፈፀመ አልነበረም።

የዘንድሮም የ2011 ውድድርን በተመለከተ በአይነቱ የተለየ ሁኔታ ተከስቷል። የ2011 አዘጋጅ ሆኖ የተመረጠው የእንግሊዝ ቡድን በአሰራር ያለመግባባትና ውስጣዊ ችግር የተነሳ ውድድሩን የማያዘጋጅ መሆኑን በደብዳቤ 20/09/2010 ለፌዴሬሽኑ አሳውቋል። ይህ በእንግሊዝ ሀገር የተከሰተው ከዚህ በፊት ገጥሞን የማያውቅ ሁኔታ ነበር። ይህም በቀላሉ የማይታይና ልዩ ትኩረትን የሚፈልግና ራሱን የቻለ መልዕክት አለው። በእርግጥ አብሮ አለመስራት መቻል በራሱ ድክመት ቢሆንም ነገር ግን ሊያመጣው የሚችለውን ችግር በመገንዘብና የለንደንንም ሆነ ባህር አቋርጦ የሚመጣውን የአውሮፓውን ህብረተሰብ አደጋ ላይ ላለመጣል ማሰብ አስተዋይነትና ትልቅነት ነው። በእርግጥ በተሸፋፈነ መልኩ እና ባወጣው ያውጣው ተብሎ ማድረግ ይቻል ይሆናል። ነገር ግን መደምደሚያውና መጨረሻው የት ነው? የዝግጅቱስ አላማ አካሄዱ ወደ የት ነው ተብሎ ሲጠየቅ ከላይ እንደተጠቀሰው አደጋ ላይ መውደቅ ይሆናልና ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ይሽላል ተብሎ የተደረገ በመሆኑ የተነሳ ነው ልዩ ትኩረት ይፈልጋል ያልነው።

- ልዩ ትኩረት ስንል የቡድኖች አቅም ግምገማ ማለት ነው።
- ልዩ ትኩረት ስንል ቡድን ዛሬ ብቅ ነገ ጥልቅ እያለ የሚታይ ሳይሆን አደረጃጀቱ ህብረተሰቡን ያቀፈና ባለበት አካባቢም እውቅናን ያገኘ ማለት ነው።
- ልዩ ትኩረት ስንል አንድ አገር የአውሮፓን ውድድር ለማዘጋጀት ጥያቄ ባቀረበበት ወቅት ከዚህ በፊቱ እንደሚደረገው ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ የአቅም መገምገሚያና መመዘናዎች ሊኖሩት ይገባል ማለት ነው።
- ልዩ ትኩረት ስንል ለውድድሩ በሰላምና በተገቢው መልኩ ስለመጠናቀቁ ዋስትና ስለመኖር ማለት ነው ይኖርበታል።

ይህንንም በተመለከተ የፌዴሬሽኑ ስራ አመራር ኮሚቴ በ23/10/2010 ስብሰባ አድርጎ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል።

## የአቋም መግለጫ

የአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን 20/09/2010 ከእንግሊዝ አትዮ - ስታር ቡድን በደብዳቤ ቁጥር 04/አትዮ - ስታር/2010 ደብዳቤው ላይ ባለው የውስጥ አለመግባባት የ2011ን ውድድር ማዘጋጀት እንደማይችሉ የሚገልፅ የቡድኑ መሪዎችና ተጨዋቶች ስም ሊስት ያዘለ ደብዳቤ ልከዋል።
የደብዳቤውም ይዘት እንደሚያብራራው የአትዮ - ስታር ቡድን አመስተርዳም ላይ በተደረገው የፌዴሬሽን ተወካዮች ጉባኤ ላይ ዕድሉን ሲሰጠን ምርጫው ስርአትን የጠበቀና ፍትህን የተከተለ እንደነበር የሚገልፅና ምን ያህል አንድ አገር ላይ ያለ ወገን ለሌላኛው ወገን የሚያስብበት ለመሆኑ ምስክርነት የሆነበትና የተደሰትንበት አጋጣሚ እንደነበር ለመግለፅ እንወዳለን። ይህንንም ያልንበት ምክንያት አብዛኛች ወገኖች የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውና የመኖሪያ ፈቃድ ቢኖራቸውም እንካን ቪዛ የማግኘት ችግር መኖሩን እያወቁ የለም ለንደኖች ጊዜያቸው ነው በማለት ስለእኛ ተጨንቀውና ተጠበው ድምፃቸውን ሰጥተውናል ይላል። በመቀጠልም ይህ ጉዳይ እናንም የበለጠ ሃላፊነት ውስጥ እንድንገባ አድርጎናል ይሉና ላለማዘጋጀት ከወሰኑባቸው ምክንቶች አራቱ እንዲህ ይላሉ።

- በውስጥ አሰራር አለመግባባትና መጓተት፣
- እኔ ከምትኩ ሰርዶ አይብቀል ብቻ ሳይሆን ነገ በመላው ህብረተሰባችን ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት፣
- ካለፉት ውድድሮች ከተከሰቱት ስህተቶች ትምህርት በመውሰድና ይህ ትልቅ ሃላፊነት እንዳይተጓጎል ደግሞም አርአያ ለመሆን በማሰብ ጭምር፣
- ስለ አውሮፓ ህብረተሰብ ሰላምና በጋራ መሰባሰብ ትልቅ ግምት ያለን በመሆኑ በማሰብ ሲሆን በመጨረሻም ወደፊት ዝግጁ በምንሆንበት ወቅት ፌዴሬሽኑ ይህን እድል እንደማይነፍገን ተስፋ እናደርጋለን የሚል ደብዳቤ ነበር።

ይህንንም ጉዳይ የፌዴሬሽኑ የስራ አመራር ኮሚቴ በ23/10/2010 በሚያደርገው ስብሰባው ላይ ሊነጋገርበት በመጠባበቅ ላይ እንዳለ በስብሰባው ዕለት ከእንግሊዝ ቡድን ተወካዮች በአገር ሽማግሌዎችና በቤተ ክርስቲያን አባቶች የተደገፈ የእርቅ መልዕክት ቀርቧል። በተጨማሪም ልዕካኑም የሽማግሌዎችን መልካም አካሄድ በመቀበል መታረቃቸውን አረጋግጠዋል በመቀጠልም የእንግሊዝ ቡድን እና የአገር ሽማግሌዎች ቡድን ቃል በመግባት ውድድሩ ወደ ለንደን እንዲመለስና በዓሉን በጋራ ማካሄድ እንደሚቻል ፌዴሬሽኑን በደብዳቤ ጠይቀዋል። ይህንንም በመለከተ ልዕካኑም ውድድሩ ለንደን ላይ ቢዘጋጅ ምንም ችግር እንደማይኖር አረጋግጠዋል። ፌዴሬሽኑም በዚሁ ቀን ከተነጋገረባቸው ዋነኛ አጀንዳ በመሆኑ በሰፉትና በጥልቀት ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፎበታል።
የሽማግሌዎችን ልፋትና ጥረት አድንቆ ለሌሎች አገሮችም ምሳሌነታቸውን አሳይተዋል ነገር ግን እርቁ ደብዳቤው ከመፃፉ በፊት ቢሆን ይመረጥ እንደነበር የፌዴሬሽን አባላት ተናግረዋል በዚህም ውይይት ላይ የፌዴሬሽኑ ህግ ማለትም

### አንድ አገር የማዘጋጀት ዕድሉን ከፌዴሬሽኑ ከተቀበለ በኋላ

- በአንድ ወር ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ብቃቱን ማሳወቅ እንዳለበት የፌዴሬሽኑ ህግ ያዛል፤
- በሁለት ወር ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ክፍያውን አጠናቅቆ ማስገባት ይኖርበታል፤

የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ ድምፅ ተሰጥቶበታል። በዚህም ድምፅ አሰጣጥ ላይ ሁለት ለሰምንት ልዩነት የውድድሩን ወደ ለንደን መመለስ የሚለውን ሃሳብ ውድቅ አድርጎታል። በዚህም ስብሰባ ላይ ለአትዮ - ስታር ቡድን ለንደን በሩ ያለተዘጋና ለወደፊቱ እራሱን በበለጠ በማዘጋጀት እድሉን እንደሚያገኝ ተብራርቷል።

## 9ኛው የአውሮፓ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን ፌስቲቫል ዝግጅት ዕጣው ምን ሆነ?

በእርግጥ እንደ ከዚህ በፊት አሰራራችን አንድ አዘጋጅ አገር ሲመረጥ በተጨማሪ አንድ ተጠባባቂ አገር አብሮ ይመረጣል። ይሁን እንጂ ተጠባባቂ አገር ዋናውን ተመራጭ አገር ተክቶ የሰራበት ጊዜ ግን አልነበረም። አሁን ያለው ሁኔታ በአይነቱ ልዩ ነውና ተሞክሮውም አዲስ ነው። ከዚህም በተጨማሪ አንድ አገር ሃላፊነትን መልሶ ለሚመለከተው ክፍል ሲያስረክብ ተረካቢው ማለትም ፌዴሬሽኑ ተጨማሪ ሃላፊነት ይወስዳል ማለት ነው። እንካን አሁን የጊዜ መጓተት ኖሮ ቀርቶ ከዚህ በፊት በታዩት ውድድሮች ላይ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ አለመጠቅም መቻል ተጨማሪ አሁን ላለንበት ሁኔታ ከላይ የተቀመጠውን የልዩ ትኩረትን ጥያቄን የሚያስነሳና ውድድሩንም ለመውሰድ በሚጠባበቁ ቡድኖች ላይ ተጨማሪ ጨና ማብዛት ይሆናል ተብሎ በማሰብ ጭምር ይሆናል። ከዚህም በመነሳት ነው የዘንድሮ ተጠባባቂ አገር የነበረው አትዮ - ኑረንበርግ ጀርመን ቡድንን በተመለከተ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል።
በውይይቱም ላይ ይህ ከፊታችን ያለውን በአይነቱ ልዩ የሆነን ከፍተኛ ሃላፊነት ካለው ጊዜና ከሃላፊነቱ ክብደት ጋር በማነፃፀር በሰፋት ተነጋግረንበታል። ካለፉት ውድድሮች ያሳለፍናቸውን ድክመቶችና ስህተቶችን መዳሰስና ተመልሰን መመልከት አሰፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባትም ነበረብን በተጨማሪም የለንደን አትዮ - ስታር ቡድንም በድጋሚ ዝግጅቱን ለማድረግ ብቃቱን በማሳወቁ ተጨማሪ ጨናና ነገሮችን በጥልቅና በጥብቅ እንድናስብ አድርጎናል። ከዚህም በመነሳት የኑረንበርግ ቡድን ምን ያህል ብቁና ይህንን በአይነቱ ልዩ የሆነንና ሃላፊነቱ ከመቸውም ጊዜ የበለጠን ዝግጅት ወስዶ ማዘጋጀት ስለመቻሉ በእርግጠኝነት መናገር ያለመቻሉና በለንደን የተከሰተው ሁኔታ እንዳይደገም በማሰብ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

**በስብሰባው ላይ ከተሰነዘሩት አስተያየቶችም ውስጥ**

- የአቅም ምዘና በተመለከተ ሲሆን የኑረንበርግ ቡድን በጀርመን አገር ውድድር ውስጥ እንካን የመሳተፍ አቅሙ ደካማ እንደሆነና እንደነበረ ከተለያዩ የጀርመን ቡድኖችና የቡድን መሪዎች የተገለፀ በመሆኑ፤
- ይህንን ትልቅና በአይነቱ ከፍተኛ ሃላፊነትን የሚጠይቅን ዝግጅትን መስጠት ማለት ቡድኑንና ህብረተሰቡን የበለጠ ችግር ውስጥ መክተትና ተጨማሪ ጨና መስጠት መሆኑና ይህም ችግር ደግሞ ሊከሰት ቢችል አሁንም ተመልሶ ወደ ፌዴሬሽኑ መምጣቱ የማይቀር መሆኑን በመረዳትና የኑረንበርግ ቡድን ባልታወቀ ምክንያት ውድድሩን ማካሄድ ባይችል እንካን ሊኖረን የሚችለውን የጊዜ እጥረት፣ የስራ ሩጨና ውጥረትን ግምት ውስጥ በማስገባት
- የ2011 ዝግጅትን በተመለከተ በተጠባባቂነት ሲመረጡ የነበራቸው ድምፅ አነስተና (2) በመሆኑ፤
- የ2010 የአመስተዳምን ዝግጅትን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርታቸው ላይ ይሆናል ተብሎ የታሰበውን ያህል መኬድ ባለመቻልና አጠቃላይ ውጤቱ አመርቂ ካለመሆን የተነሳና ይህንን ልዩ ትኩረት የሚጠይቅን ዝግጅት ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚኖርብን የሚሉ አስተያየቶች ነበሩ።
- በጠቅላላ ድምፅ ይህ አይነቱ አካሄድ መቆም እንዳለበት ስለታመነም ጭምር ነው።

ከዚህም በመነሳት ፌዴሬሽኑ ለዝግጅቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት የዚህን አመት ማለትም የ2011 ውድድርን በክለቦች ታግዞ ማዘጋጀት እንዳለበት ሃሳብ ቀርቦ ስራ አመራሩ ተስማምቷል።
ይህም የታሰበበት ዋነኛ ምክንያት እስከ ዛሬ በተደረጉት ውድድሮች ሁሉ ውድድሩ ካለፈ በሃላ የመጀመሪያ ተወቃሽ ፌዴሬሽኑ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ፌዴሬሽኑም ይህም እየሆነ ከነገ ዛሬ ለውጥ ይኖራል በማለት እስከ ዛሬ ድረስ በመታገስ የቆየ ሲሆን በሂደቱም ሁኔታዎች እየተሻሻሉ የመጡ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ ውድድሩ ስጋት ላይ እየወደቀ የመጣ መሆኑን ያሳያል። ለመጥቀስም ያህል፤

## <u>የፌዴሬሽኑ የ9 አመታት ዝግጅቶችና ተሞክሮ ምን ይመስሉ ነበር?</u>

- ከብዙሃኑ ይልቅ የጥቂቶች መጠቀሚያ ሆኖ ታይቷል፤
- በቡድኖች መካከል ከመጋጨት ሌላ የታየ መሰረታዊ ለውጥ የለም፤
- በቡድኖችም ሆነ በህብረተሰቡም ላይ አለመግባባትን ፈጥሮ አልፏል፤
- ስፖርተኛውም ሆነ ተመልካች ተበዳይ የሆነበትና ቅሬታውን ያሰማበት ሆኖ ታይቷል፤

አንደኛው ከአንደኛው በጥቂቱ የተሻለ ቢመስልም ሃላፊነቱን በሚገባ የተወጣና የገባውን ቃል የፈፀመ አልነበረም። በዚህም ሳቢያ ብዙ ክለቦች ፈርሰዋል፣ ሲበጣጠሱና ሲከፋፈሉ የታየበት ሁኔታዎች በመሆኑ የዘንድሮን ዝግጅት ፌዴሬሽኑ አዘጋጅቶ ማሳየት እንዳለበት ውሳኔ ላይ ተደርሷል።

## ውድድሩን ፌዴሬሽኑ የማዘጋጀቱ ጥቅም፣ አላማና ዕቅድ፤

- የስፖርት ውድድሮችም ሆነ ፌስቲቫሉ አደጋ ላይ እንዳይወድቅና በተገቢው መልኩ እንዲሄድ ለማድረግ፤
- የወጣቶች ውድድርን በበለጠ ለማጠናከር፤
- በእጅጉ ደክሞ ያለውን የባህል ዘርፍ ለማጠናከር፤
- የቴክኒክ ዘርፉን በበለጠ ለማጠናከር፤
- ከእግር ካስ ባሻገር የተለያዩ ስፖርቶችን ለማዋቀር፤
- የሴቶች ውድድሮችን ለማዋቀር፤
- አትዮጵያ ወክሎ ሊወዳደር የሚችል አንድ የተወጣጣ ቡድን በማዘጋጀት በሆላንድ በየአመቱ በሚዘጋጀው የአለም አማተር እግር ካስ ውድድር ላይ እንዲሳተፍ ለማድረግ፤
- በአሜሪካ በሚደረገው የአትዮጵያውያን እግር ካስ ውድድር ላይ ተሳታፊ የሚሆን ቡድን
- በስፖርት ዙሪያ የብዙሃኑን መብት የሚጠበቅበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት፤
- በስፖርቱ ዙሪያ የሚገኝ ማንኛውንም ጥቅም ስፖርተኛውና የስፖርት ማህበሩን በተገቢው መልክ እንዲገለገልበት ለማድረግ፤

## ውድድሩ የት መሆን አለበት?

ይህንንም በተመለከተ ብዙ አነጋግሯል። ልክ የፌዴሬሽኑን የ9 አመታት ተሞክሮ ወደ ኋላ መለስ ብለን እንደተመለከትነው ሁሉ የፌዴሬሽኑን አመሰራረት መለስ ብለን መመልከትም አስፈላጊ ነው። ዛሬ ያለንበትን ብቻ ሳይሆን ከየት ተነስተን የት እንደደረስን መመልከቱ አስተዋይነትና ሰዎች ለጠነሰሱት ለመልካም ሃሳቦቻቸውና ለሰሩት መልካም ስራቸው ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በማሰብም ጭምር ነው። የሃሳብ ትንሽ የለውም የብዙ ጥቃቅን ሃሳቦች ለትላልቅ ስራዎች መንስአ ሆነው ይታያሉ። እናም ዛሬ ስለፌዴሬሽናችን ጥንስስ ስንናገር ጥቂቶች ተሰብስበው የጠነሰሱት መልካም ስራ ለዛሬ ለእና በሰፊው መገናኛን ፈጥሮልናል። የእዚህ ጥቂት መልካም ሰዎች ጅምር ዛሬ ብዙ ሰዎችን አገናኝቷል። ይህ የጥቂቶች ጅምር ስንቶችን በትዳር አስተሳስሯል ብሎም አዋልዷል አካብዷል። ይህ ጥንስስ ታሪክ ነው ፣ታሪክ ደግሞ ቅርስ ነው ቅርስ ደግሞ መረሳት ያለበት ሳይሆን ሁሌና በተገኘ አጋጣሚ መታወስ የሚገባው ነገር ነው። ከዚህም በመነሳት ነበር ይህንን ልዩ ትኩረትን የሚጠይቅ ታሪካዊ ዝግጅት ከታሪኩ ጠንሳሾች ጋር ማዛመድ የተፈለገውና የመጀመሪያዎቹ ጠንሳሽ አገሮች ማለትም ፍራንክፈርት ጀርመን፣ ፈረንሳይ እና ሆላንድ ላይ ትኩረት የተደረገው በመቀጠልም ከሶስቱ ጠንሳሽ አገሮች መካከልም የመጀመሪያው ስብሰባቸው በፍራንክፈርት ከተማ ያደረጉና በሶስቱም ቡድኖች መካከልም የእርስ በእርስ መተዋወቂያ ዝግጅት ማድረጋቸው ከዛም ይህ ስብሰብ ዛሬ አድጎ ከሶስት አልፎ እስከ ሀያ ሶሶት ቡድኖችን ያቀፈና የህብረተሰቡም ቁጥሩ እጥፍ ድርብ የሆነበት ምክንያቶች ናቸውና ዛሬም ይህ ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጀው ዝግጅት ጥንስሱ በተጀመረበት አገር ላይ ማድረጉ ጥንስሱን የጀመሩት ቡድኖችን ስለ አደረጉት መልካም ስራቸውን የምናስታውስበት ይሆናል። ከዛም በተጨማሪ ፍራንክፈርት አማካኝና እምብርት ስለሆነና የፌዴሬሽኑ የስራ አመራር አባሎች ስለሚገኙና በቅርብም ሆነ ሁኔታውን መከታተል ስለሚቻልም ታስቦ ነው። ይህንንም ውሳኔ በሚመለከት የ15 ቀን ጊዜ የተሰጠና የደረሱበትን ሁኔታ ለፌዴሬሽኑ በአስቸካይ እንዲያሳውቁ ይህ ካልሆነ ግን ውድድሩ ሌላ አገር ላይ እንደሚደረግ በሙሉ ድምፅ ተቋጭቷል።

## መደምደሚያ፤

ሃላፊነት ከሸክም ይከብዳል ይባል የለ የሃላፊነት ትንሽ የለውም። በሃላፊነት መቀለድ የለም በሃላፊነት መቀለድ ማለት በህዝብ ላይ መቀለድና የተሰጠን አደራ በአግባቡ አለመወጣት ማለት ነው። አደራን በተገቢው መልኩ መወጣት አለመቻል በብዙሃን ላይ ሊያመጣው የሚችለው ችግር ወደር የለሽና አስከፊነቱ የበዛ ሊሆን ስለሚችል የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ሚዛናዊና ማዕከላዊነትን የያዘ ቢሆን ከተጠያቂነት ሊያድን ይችላል። በእርግጥ ሁኔታዎች ለሁላችንም በፈለግነው መንገድ ሊሆኑልን አይችሉ ይሆኑና ሰዎች በመሆናችን ቅሬታ ይሰማን ይሆናል። ነገር ግን ትልቁን ተልዕኮዋችንን በመመልከት በአንድ ላይ መጓዝ የተሻለና ዛሬን ሳይሆን ከዛሬ ባሻገር መመልከቱ የሚበጅ ይመስላል። ይህ ዛሬ የተወሰደው አቋም ለነገ ጥሩ መሰረትን መገንባት እንዲያመች ነው። ይህ ዛሬ የምንወስደው አቋም ነገም እንደዛሬ ባዶ ሆና እንዳታልፍ በማሰብ ነው። ይህ ዛሬ የምንከፍለው ዋጋ የነገውን ትውልድ እንዲያረጋጋ ታስቦ ነው። ይህ ዛሬ የምንከፍለው መስዋዕነት የነገውን ትውልድ ከዕዳ ነፃ ለማውጣት። ይህ ዛሬ የምንከፍለው መስዋዕትነት ለነገው ወጣት ትምህርት ለመስጠት፣ ለማስተማር ሃላፊነት ነውና የእና ዛሬ መጎዳት መቻቻልና ሆደ ሰፊነት ይጨመርበት እያልን ወገናዊ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።

መተሳሰብ፣ መተባበር፣ቅንነት ትልቁ ባህላችን ይሁን።

ESCFE: Sint Willibrordous Straat 23, 1074 XJ Amsterdam, Netherland.
Telephone: 0031206892205 / 0031614867346
www.escfe.org / www.escfe.net